# ዝነኛነትን መሸከም አለመቻል እና የዝና ሱስነት

(ከአብዱራህማን አህመዲን፣ የቀድሞ የፓርላማ አባል)

*(ይህ ጽሑፍ ዛሬ ነሐሴ 1 ቀን 2005 በወጣው ሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ታትሟል፡፡ ጋዜጣውን የማያገኙ፣ በተለይም በውጭ ሀገር ያሉ ዜጎች ሁሉ ቢያነቡት 'ይጠቅማል፤ ለመወያያም መነሻ ሊሆን ይችላል' በሚል መንፈስ በአይጋ ፎረም ድረ-ገጽ በኩል እንዲታተም ተልኳል፡፡)*

ባለፈው ሰሞን በዚሁ በሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ለአንድ "ፖለቲከኛ" 'ይድረስ' ብዬ የጻፍኩት መጣጥፍ ርዕስ "የፖለቲከኞቻችን ዝናና ክብርን መሸከም ያለመቻል መርገምት..." የሚል እንደነበር ይታወሳል፡፡ ያንን ጽሁፍ ያነበቡ አንዳንድ ወዳጆቼ " '...ዝናና ክብርን መሸከም አለመቻል...' ስትል ምን ማለትህ ነው?... ሃሳቡን ሰፋ አድርገህ ብታብራራው ጥሩ ነበር... " የሚሉ ተደጋጋሚ አስተያየቶችን አቀረቡልኝ፡፡ ይህንንም አስተያየት መነሻ በማድረግ ተጨማሪ ሰነዶችን ፈተሽኩ፡፡ የመረጃ መረቦችን በረበርኩ፡፡ '...ዝናና ክብርን መሸከም ስላለመቻል ብቻ ሳይሆን ስለ ዝና ሱስነት ጭምር መጠነኛ ቅኝት አደረግኩ፡፡ እናም ይህቺን ጽሁፍ አዘጋጀሁ፡፡

እንደሚታወሰው ባለፈው ጽሁፌ ላይ ትኩረት ያደረግኩት በፖለቲከኞቻችን ዝናና ክብርን መሸከም አለመቻል ዙሪያ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህ ዝናና ክብርን መሸከም ያለመቻል ጉዳይ በፖለቲከኞች ዙሪያ የታጠረ ሳይሆን፤ በስፖርተኛው፣ በሙዚቀኛው፣ በጋዜጠኛው፣ በባለሀብቱ፣... ወዘተ. ጭምር ላይ የሚስተዋል የህብረተሰብ ችግር ነው፡፡

ሰዎች ዝነኛነትን (fame) በተለያዩ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ሊጎናጸፉ ይችላሉ፡፡ ጥሩ ስፖርተኛ፣ ሸጋ ሙዚቀኛ፣ ስመ-ጥር ደራሲ፣ አንደበተ ርቱዕ ፖለቲከኛ፣ ሐቅ ፈልፋይ ጋዜጠኛ፣... ወዘተ. በመሆን ዝናን መጎናጸፍ ይቻላል፡፡ አንድ ህብረተሰብ ከውስጡ ለወጡ 'ዝነኞች' 'እውቅና' ይሰጣል፡፡ ይህም 'እውቅና' (Recognition) በግጥም ከማወደስና በዘፈን ከማነሳሳት ጀምሮ እስከ "ፈርሙልን" በሚዘልቅ ሁኔታ ሊገለጽ ይችላል፡፡ የእውቅናው "ሰርተፊኬት" ደግሞ "ለዝነኞቹ" በሚሰጥ አክብሮት እንደሚረጋገጥም አስባለሁ፡፡

እዚህ ላይ "ለመሆኑ ይህ ዝናና ክብርን መሸከም ያለመቻል ችግር በምን መልኩ ነው የሚገለጸው?" የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ እንደሚችል መገመት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ፡- አርቲስቶቻችን፣ ፖለቲከኞቻችን፣ ስፖርተኞቻችን፣... ወዘተ. ህብረተሰቡ "ጎሽ፣ አበጃችሁ" ሲላቸውና በሚያልፉበት በሚያገድሙበት ሁሉ 'የት ነው የማውቀው?' በሚል መንፈስ ትኩር ብሎ ሲመለከታቸው ልባቸው ማበጥ ይጀምራል፡፡ በጊዜ ሂደት ነገሩ ሲደጋገም፣ ሰው ሁሉ የሚያውቃቸውና የሚያደንቃቸው ስለሚመስላቸው መንፈሳቸው ሰማየ ሰማያት ተመንጥቆ ይሄዳል፡፡ አንዳንዱ ደፋር ድንገት ጨብጧቸው አድናቆቱን ሲገልጽላቸውና ከዚያም አለፍ ብሎ "ፈርምልኝ ወይም ፈርሚልኝ" ማለት ሲጀምር ደግሞ 'ከእኔ በላይ ማንም የለም!' የሚለው መታበይ ይከተላል፡፡ እብሪት መጠን ያልፋል፡፡

በተገኙበት ምግብ ቤት ወይም ካፌ ለበሉትና ለጠጡት 'ሂሳብ ተከፍሏል' ሲባሉ፣ እንዲሁም የተቃራኒ ፆታ የፍቅር ጥያቄው ብቅ ብቅ ማለት ሲጀም ሁሉም ነገር ድብልቅልቁ ይወጣል፡፡ በየአደባባዩ ድፍረት የተሞላበት የንቀትና የእብሪት ንግግር ወይም ቃለ ምልልስ ይንጸባረቃል፡፡ ዓለም በሙሉ ስለእነርሱ የሚያወራ ይመስላቸዋል፡፡ ዓለም በሙሉ እነርሱ የሚያደርጉትን ንግግር

የሚያዳምጥ፣ የጻፉትን የሚያነብ ይመስላቸዋል፡፡ በተለይ ፖለቲከኞች በአንዲት ጠባብ መድረክ ላይ ባደረጉት ንግግር የሚሰሙት ጭብጨባ በመላ ሀገሪቱ ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚያስተጋባ ይመስላቸዋል፡፡ በዚህም "አገር ነቅንቀ ንግግር" ማግስት ሕዝብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ መንግስት እንደሚገለብጥ ያስባሉ ወይም ይመኛሉ፡፡

እንዲህ ዓይነት እሳቤ የነበራቸውን ግብዝ ፖለቲከኞች በአስራ ሁለት ዓመታት የፖለቲካ ሕይወቴ አስተውያለሁ፡፡ ከምርጫ 97 በኋላ አንድ 'ጎምቱ የፖለቲካ ጉሩ' የፈጸሙትን ተግባር እዚህ ላይ ብጠቅሰው ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡ እንደሚታወቀው ከምርጫው በኋላ በቅንጅት ውስጥ ሰፊ የሃሳብ ልዩነት ተፈጥሮ ነበር፡፡ ቅንጅት የችግር አፈታት ስርዓት ስላልነበረው "የፓርቲው" አመራርም፣ ደጋፊውም እንዳሻው ይናራል፡፡ ከመሬት ተነስቶ አንዱን ያወግዛል፣ ሌላኛውን ይደግፋል፡፡ ሁሉም እንዳሰኘው ይፏልላል፡፡

በወቅቱ ከሌሎቹ የቅንጅት አመራሮች ያፈነገጠ ሃሳብ የነበረን ከኢዴፓ የመጣን 'ጥቂት' ወጣቶች ነበርን፡፡ ይህንን ያስተዋሉ አንድ በእውቀታቸው የመጠቁ፣ በልምዳቸው የበቁ፣ ታላቅ ስም የደረቡ፣ በአንጋፋነታቸው የተካቡ "የፖለቲካ ሰው" አንዱን የኢዴፓ አመራር ቤታቸው ድረስ ይጠሩትና "እከሌ የተባለው ጓደኛህ በ24 ሰዓታት ውስጥ አሁን የያዘውን አቋም ካላቆመ በጋዜጦች ላይ ወያኔ ነው ብየ እጽፍበታለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ ሕዝብ አንቅሮ ይተፋዋል፡፡ የእሱ ነገር ያልቅለታል…" የሚል መንፈስ ለው የማስጠንቀቂያ ይሁን የማስፈራሪያ መልእክት ማስተላለፋቸውን አስታውሳለሁ፡፡

እኒሁ ሰው በአንድ የቅንጅት አመራር ስብሰባ ላይ "ወያኔ ስልጣኑን ያስረክብ እንጂ በትግራይ ሕዝብ ላይ ምንም ነገር እንዳይደርስበት እኔ በመገናኛ ብዙሃን ወጥቼ ዋስትና (Guarantee) እሰጣለሁ" ማለታቸውንም በዚያው ሰሞን ሰምቼ ነበር፡፡ ለአምስት ሚሊዮን ሕዝብ አንድ ግለሰብ ዋስትና ሲሰጥ ይታያችሁ!! እንግዲህ እኔ "ዝናና ክብርን መሸከም አለመቻል" የሚል ስያሜ የሰጠሁት እንዲህ ያለውን የትምክህት ንግግርና መታበይ የሚስተዋልባቸው ድርጊቶች ነው፡፡

በኔ እምነት ሕብረተሰቡ 'አንቱ' ብሎ ከበሬታን ያጎናጸፋቸው ታዋቂ ግለሰቦች የሚፈጽሟቸው ተግባራትም ሆኑ የሚያራምዷቸው ሃሳቦች ጥንቃቄ የተደረገባቸው፣ ቀጣይ የህዝብ አመኔታን የሚያረጋግጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ያን ካላደረጉ ግን ለዓመታት ባደረጉት ጥረት ያገኙትን ክብርና ዝና በአንድ ዠንበር የሚያጡበት፣ ወደ ትቢያ የሚወረወሩበትና ዓይንህን ለአፈር የሚባሉበት ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ ይህንን በዚሁ እንተወውና ለመሆኑ "ዝና ሱስ ይሆናል?" የሚለውን ጥያቄ እንይ፡፡

ይህንን ጸሁፍ ለማዘጋጀት ስነሳ በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ አንዳንድ ሰነዶችን ለማየት ሞክሬአለሁ፡፡ በተለይም "እውን ዝና ሱስ ይሆናል?" (Is Fame addictive?) የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የዘመኑን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የኢንተርኔት አሰሳ (Google) አድርጌአለሁ፡፡ የፍለጋየን ውጤት ለማሳየት ከመሞከሬ በፊት ለመንደርደሪያ የሚሆነኝን አንድ ጉዳይ ላስቀድም፡፡

*(አንድ ሰው ሃሳቡን በተጠናከረ ሁኔታ ለማስረዳት የሚችለው ያየውን፣ የሰማውንና በተግባር የተሳተፈበትን ሁኔታ በተጨባጭ እየጠቀሰ ሲያቀርብ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ እናም ከዚህ የሚከተለውን ሃሳብ የማቀርበውም ከዚህ ድምዳሜ በመነሳት መሆኑን አስቀድሜ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡)*

ከምርጫ 97 በኋላ በቅንጅት ውስጥ ተከስቶ የነበረውን ልዩነት በተመለከተ ከበርካታ ሰዎች ጋር ተወያይቻለሁ፣ ተከራክሬአለሁ፡፡ በወቅቱ የልዩነት ሃሳብ ከነበራቸው አመራር አባላት አንዱ እንደመሆኔ በክርክሩና በውይይቱ ሂደት የማቀርባቸውን ሃሳቦች ማሸነፍ ያቃታቸው አንዳንድ ሰዎች "አንተ ከእነ ዶ/ር እከሌ፣ ፕሮፌሰር እንቶኔ፣... በልጠህ ነው? እነሱኮ ፖለቲካ ውስጥ የገቡት ብር ብለው ወይም ስልጣን ፈልገው አደለም፡፡ አገራቸውን ብለው ነው..." የሚል መከራከሪያ ያቀርቡልኝ ነበር፡፡ በወቅቱ ለዚህ ሃሳባቸው አቀርብ የነበረው መልስ ደግሞ "አዎ! እንዳላችሁት ብርም እውቀትም ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ስልጣንም አንፈልግም ሊሉ ይችላሉ፡፡ ...እነዚህ ሰዎች ግን በአፄ ኃ/ስላሴ፣ በደርግ፣ ዛሬም በኢህአዴግ የስልጣን ዘመን በሀገሪቱ ፖለቲካ ላይ ብቅ ጥልቅ የሚሉት ዝና ሱስ ስለሆነባቸው ነው" የሚል ነበር፡፡

ይህ ንግግር ብዙዎችን ይበልጥ በንዴት ያጦፋቸው ነበር፡፡ እኔ ይህንን ሃሳብ እሰነዝር የነበረው በወቅቱ በታይም መጽሔት ላይ የቀረበን ጥናታዊ ጽሁፍ መነሻ በማድረግና ስማቸው ከተጠቀሰው የቅንጅት አመራር የሆኑ ኢንጂነሮች፣ ፕሮፌሰሮችና ዶክተሮች... ስነ-ምግባር ጋር በማነጻጸር በመረጃ ላይ በመመስረት ነበር፡፡ ከዚያም ወዲህ ያገኘኋቸው መረጃዎች ዝና (Fame) ልክ እንደ ቡና፣ ልክ እንደ መጠጥ (አልኮል)፣ ልክ እንደ አደንዛዥ እፅ፣... ሱስ የመሆን ባህሪ ያለው መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

ይህንን በተመለከተ በተለያዩ የአውሮፓና የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የሥነ-ልቦና ተመራማሪዎች ዝና ፈላጊነትንና የዝና ሱስነትን በተመለከተ የምርምር ውጤታቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡ ከነዚህ የምርምር ውጤቶች ውስጥ የተወሰኑትን አጠር አጠር አድርጌ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

ዶክተር አዳም ጆንሰን የተባለ የሥነ ልቦና ተመራማሪ ማክስ ክሊፎርድ የተባለውን እውቅ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ በማነጋገር እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ ባቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ እንዲህ ብሎ ነበር "ዝና ልክ እንደ አደንዛዥ እፅ ነው፡፡ ሱስ ይሆናል፡፡ ሰዎች ይዘፈቁበታል፡፡ ይራቡታል፣ ይጠሙታል፡፡ ይሁን እንጂ መጠኑ ከሰው ሰው ሊለያይ ይችላል፡፡ ...አደገኛ ሱስ ነው፡፡ ማህበራዊ ኑሮን ያቃውሳል፡፡ አስተሳሰብን ያዛባል፡፡ ...ትልቅ ቤት፣ ትልቅ መኪና፣ ... ብዙ ትልልቅ ነገርን ያስመኛል፡፡ ራስን ከተራው ህብረተሰብ መለየትና ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ ዋነኛ መገለጫው ነው፡፡ ... እዚህ ደረጃ ላይ ሲደረስ ራስን ማስተካከል ካልተቻለ በህብረተሰቡ ዘንድ መገለል ሊከተል ይችላል..."

ዶክተር ሪፍ ከሪም የተባሉ የሥነ-ልቦና ተመራማሪ ባደረጉት ጥናት ሰዎች ዝነኛ ለመሆን ዝናን (Famous for being famous) የመፈለግ ባህል እየተፈጠረ ነው ይላሉ፡፡ ዶክተር ዴቪድ ዊልሰን የተባሉ አንትሮፖሎጂስት በበኩላቸው "ዝናን የመፈለግ [አባዜ] ልክ እንደ ምግብ ፍላጎታችን ልንቆጣጠረው የማንችለው..." ሱስ እየሆነ መጥቷል የሚል ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡

"ዝና የአጭር ጊዜ ቆይታ ያለው ነገር ነው፡፡ እናም ታዋቂ የሆኑ ሰዎች እናጣዋለን፣ ዘወር ብሎ የሚያየን አይኖርም፣... የሚል ስጋት ያድርባቸዋል፡፡ በመሆኑም እሱን ላለማጣት ጧት ማታ ይባዝናሉ..." የሚሉት ደግሞ ዶክተር ሮቢ ሉድዊግ የተባሉ ተመራማሪ ናቸው፡፡ ዶክተር ዶና ሮክዌል የተባሉ የሥነ-ልቦና ጠቢብ በበኩላቸው እንዲህ ብለዋል፤ *"The lure of adoration is attractive, and it becomes difficult for the person to imagine living without fame."*

በአጠቃላይ በአንድ አጋጣሚ ዝነኛ የሆኑ ሰዎች ከመድረክ ላይ ከጠፉ ዓለም የዘነጋቸው፣ ሕዝብ አንቅሮ የተፋቸው ስለሚመስላቸው በውስጣቸው የሚፈጠረው ጭንቀት እጅግ የበረታ ነው፡፡ እናም ይህንን ጭንቀታቸውን ለማብረድ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መድረክ ላይ ብቅ ማለትን ይመርጣሉ፡፡ ከላይ የጠቀስኳቸው በዘርፉ የተመራመሩ ጠቢባን እንደሚሉት ዝና ሱስ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ በአስራ ሁለት ዓመታት የፖለቲካ ተሳትፎየ ያጋጠሙኝ ሁኔታዎችም በተጨባጭ ያረጋገጡልኝ እውነታ ይህንኑ ነው፡፡

ብዙዎቹ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ ፖለቲከኞችን የኋላ ታሪክ ብንፈትሽ በቁጥር ጥቂት የማይሰኙት ከአንዱ ፓርቲ ወደ ሌላ እየተገላበጡ አሁን ያሉበት ደረጃ መድረሳቸውን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ እስከ አምስት ፓርቲ የቀያየሩ ግለሰቦችን አውቃለሁ፡፡ ይህ ሁሉ መገለባበጥ የተከሰተው የዝና ሱስ ስለተጠናወታቸው እንጂ የያዙትን ዓላማ ለማሳካት ቢሆን ኖሮ መጀመሪያ አባል በሆኑበት ፓርቲ (ችግር ቢኖርም በውይይት እየፈቱ) ይቀጥሉ ነበር፡፡

የሀገራችንን የፖለቲካ እንቅስቃሴ የጎዳው እንዲህ ያለው የግለሰቦች ዝና ፈላጊነት ይመስለኛል፡፡ ከምርጫ 97 በኋላ ያስተዋልኩትን አንድ አጋጣሚ እዚህ ላይ ባነሳው ጥሩ ማሳያ ይመስለኛል፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ ቅንጅት ፓርላማ እንግባ - አንግባ በሚለው አጀንዳ ዙሪያ የበላይ አመራረሩ ውይይት ባደረገበት ወቅት "እንግባ" የሚለውን ሃሳብ ያቀነቅኑ የነበሩ ሰዎች አሳማኝ የመከራከሪያ ሃሳብ እንዳላቀረቡ ራሳቸው ጭምር ይገነዘቡት ስለነበር፣ ውሳኔው በሚስጢራዊ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት እንዳይካሄድ አጥብቀው ተከራከሩ፡፡ (በሚስጥር ከተካሄደ ብዙሃኑ እንግባ የሚለውን ሃሳብ እንደሚደግፉ ይታመን ነበር)

በዚህ ወቅት አንድ ከመኢአድ የተወከሉ 'የፖለቲካ ሰው' የሰጡት አስተያየት "ድምጥ አሰጣጡ ሚስጢራዊ መሆን የለበትም፡፡ ማን እንግባ እንዳለ፣ ማን አንገባም እንዳለ ለሕዝባችን መታወቅ አለበት፡፡ ...ነገ ባደባባይ ደረታችንን ነፍተን ለመሄድ ውሳኔአችን 'አንገባም!' የሚል መሆን አለበት" የሚል ነበር፡፡

ለእኚህ 'የፖለቲካ ሰው' ወሳኙ ነገር ፓርላማ በመግባት ወይም ባለመግባት የሚገኘው የፖለቲካ ግብ ሳይሆን፣ የስሜታዊ ደጋፊዎቻቸውን ቀልብ የሚስብ ውሳኔ በማሳለፍ በአደባባይ ደረትን ነፍቶ መሄድ ነው፡፡ እንዲህ ያለው የስሜታዊነት መንገድ የፖለቲካ ብስለትን ሳይሆን ተራ ዝና ፈላጊነትን የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ የሀገራችን የተቃውሞ ፖለቲካ እንዲህ የተሸመደመደውም በጠለቀ የርእዮተ-ዓለምና የፖለቲካ ግንዛቤ ላይ ሳይሆን፣ በእንደዚህ ዓይነት የግለሰቦች ዝና ፍላጎት ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ ይመስለኛል፡፡

ጽሁፌን ለማጠቃለል ያህል አንዳንድ ነጥቦችን አነሳለሁ፡፡ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው አንዳንድ ፖለቲከኞቻችን "ሕዝብ" የሰጣቸውን ክብርና ዝና በአግባቡ መሸከም አይችሉም፡፡ ፖለቲከኞቹ ብቻ ሳይሆኑ ሙዚቀኛው፣ ሰዓሊው፣ አትሌቱ፣ ስፖርተኛው፣ ገጣሚው፣ ጋዜጠኛው፣... ወዘተ. ከ"ሕዝብ" የተሰጣቸውን አድናቆትና አክብሮት በአግባቡ ተቀብለው ማስተናገድ የማይችሉበት አጋጣሚ ይስተዋላል፡፡ ባለሃብቱ የገንዘቡ መጠን እየጨመረ ሲመጣ "ከእኔ በላይ..." የሚል እብሪቱ ልክ ያጣል፡፡ የሀብቱ መብዛት ያስገኘለትን "እንቱታ" መሸከም አቅቶት ሲሸመደመድ ይታያል፡፡

በጥቅል አነጋገር ብዙ ወገኖችን እንዳላስቀይም እየሰጋሁ ነው እንጂ አንዳንድ ጊዜ "ብዙዎቻችን ኢትዮጵያውያን ዘለቄታ ያለው ውጤት ላይ ለመድረስ ሳንችል በየመንገዱ ተሰነካክለንና

ተንጠባጥበን የምንቀረው በየአጋጣሚው የምናገኘውን ክብርና ዝና መሸከም ባለመቻላችን ነው” የሚል ሃሳብ ብልጭ ይልልኛል፡፡ በርግጥ በሽታው ሁላችንም ላይ የሚስተዋል መሆኑ የሚታበል አይመስለኝም፡፡ ዝና ደግሞ ሱስ መሆኑ የሚያጠራጥር አደለም፡፡ ፈውሱ ቀላል ነው - ለበሽታው እውቅና ሰጥተን ራሳችንን መፈተሽ ብቻ!!!